# ወርሃዊ የአየር ጠባይ ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከዲሴምበር ከ1-31/2022 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ እንዲሁም

## ከጃንዋሪ 1-31/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጃንዋሪ 2023
አዲስ አበባ

**ርዕስ** **ገፅ**


እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ ........ 3

ካርታ 7 ከዲሴምበር 1-31 የነበረው ዝቅተኛ የቀኑ የሙቀት መጠን በዲግሪ ሴልሺስ ........ 4

ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ 5

ካርታ 9 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ........ 6

ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው........ 7

ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ........ 7

እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ........ 8

ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ 8

ካርታ 11 ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ 8

እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ 9

ካርታ 12 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ 9

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2023 የሚኖረው የአየር ........ 10

ጠባይ አዝማሚያ ........ 10

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 10


እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 11

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

ባለፈዉ የዲሴምበር ወር ደረቅ፣ ፀሃያማ እና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በተለይም በመጀመሪያዉና ሁለተኛዉ አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ተጠናክሮ የተስተዋለ ሲሆን፤ የሌሊትና የማለዳዉም ቅዝቃዜ በአንዳንድ የሰሜን፣ መካከለኛዉ፣ ደቡብና ምስራቅ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ አይሎ ተስተዉሏል፡፡ በተጨማሪም የቀኑ ዝቅተኛ ሙቀት በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ለአብነት ያህል አደሌ -4.0 እና -4.0፣ በደብረብርሀን -0.8፣ 1.4፣ 4.2፣ 3.6፣ 3.2፣ 4.8 እና 3.0 ፤በሐሮማያ 0.6፣ 0.2፣ 2.0፣ 1.8፣ 2.4፣ 1.0፣ 1.8፣ 1.8 እና 2.4፤ በቡኢ 4.0፣ 3.0፣ 4.0፣ 4.5፣ 4.0፣ 4.6 እና 4.0 ፤በጨፋ 2.4፣ 2.8፣ 3.0፣ 2.4፣ 3.2፣ 2.4፣ 3.4፣ 3.6፣ 4.8 እና 4.2፤ በአደሌ 4.0፣ 2.5፣ 2.2፣ 4 እና 4.5 ፤በመሐል ሜዳ 2.2፣ 2.8፣ 3.2፣ 4.5፣ 4.2፣ 4.8 እና 2.2 ፤አርሲ ሮቤ 4፣ 4.5፣ 4.5፣ 4፣ 4 እና 3.0፤ ዳንግላ 4.6፤ ደባርቅ 4.5፣ 4.5 እና 4.4፤ ደብረ ወርቅ 4.8 እና 4.8፤ጅማ 4.5 ፤ሮቤ 3.4፣ 3.6፣ 4.2 እና 4.4 ፤ነቅምት 1.0 ፤የትኖራ 4.1 እንዲሁም በወገል ጤና 4.5፣ 4.0፣ 4.0፣ 2፣ -0.2፣ 1.4፣ 2.6፣ 3.2፣ 2.6 እና 3.2 በዲግሪ ሴልሽየስ መመዝገቡን ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል (ካርታ 7)፡፡ ይሁን እንጂ በዲሴምበር የመጨረሻዎቹ አስራ አንድ ቀናት አንፃራዊ የሆነ የደመና ሽፋን በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ተስተዉሏል፡፡ በመሆኑም የሌሊትና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ ጋብ ብሎ ተስተዉሏል፡፡ በተጨማሪም ከነበረዉ የደመና ሽፋን በአንዳንድ የደቡብ ምዕራብና የሰሜን የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡


ባለፈዉ የዲሴምበር ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም ከአማራ የሰሜን፣ መካከለኛውና የደቡብ ጎንደር፣ ባቲ፣ የዋግህምራ፣ የሰሜንና ደቡብ ወሎ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ በኢሉባቦር፣ በጅማ፣ በሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ በሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ በደቡብ ቦረና፣ በአርሲና በቡኖ በደሌ ዞኖች፤ በጋምቤላ፤ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በከማሺ ዞን፤ ከአፋር በዱብቲና በሰመራ ዞኖች፤ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እንዲሁም በአብዛኛው የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ዞኖች ላይ ከ5-137 ሚሜ የሚደርስ ከ2-15 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 8 እና 9) ፡፡

ባለፈዉ የዲሴምበር ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከአማራ የሰሜን፣ መካከለኛውና የደቡብ ጎንደር፣ ባቲ፣ የዋግህምራ፣ የሰሜንና ደቡብ ወሎ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ በኢሉባቦር፣ በጅማ፣ በሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ በሰሜን ሸዋ፣ በአርሲና ባሌ ጥቂት ቦታዎች ላይ፤ ከአፋር ክልል በዱብቲና በሰመራ ዞኖች፤ በጋምቤላ፤ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እንዲሁም አብዛኛው የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ዞኖች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን የነበራቸዉ ሲሆን፤ የተቀሩት የወቅቱን ዝናብ ማግኘት የሚገባቸው የደቡብና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎችን ጨምሮ ደረቅ ሆነው ሰንብተዋል (ካርታ 10) ፡፡





ካርታ 7 ከዲሴምበር 1-31 የነበረው ዝቅተኛ የቀኑ የሙቀት መጠን በዲግሪ ሴልሺስ


## ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 9 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የዲሴምበር ወር የነበረው የአየር ጠባይ ለወቅታዊ የግብርና እንቅስቃሴ አንጻር ሰብል ለመሰብሰብና የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለማከናወን አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበር። በወሩ መጨረሻ ቀናት ከነበረዉ የደመና ሽፋን በአንዳንድ የደቡብ ምዕራብና የሰሜን የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ በመኖሩ አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት የእርጥበታማ ሁኔታው በአመዛኙ ነበራቸው። ይህም ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ እድገታቸውን ላልጨረሱ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም በመኸር ወቅት መጨረሻ ላይ ለሚዘሩ ሰብሎች ጠቀሜታ የነበረው ቢሆንም በአንዳንድ ስፍራዎች በደረሱና በመሰብሰብ ሂደት ውስጥ ባሉ ሰብሎች ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ነበረው (ካርታ 11)፡፡


ካርታ 11 ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው ዲሴምበር ወር የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረውን ገፅታ ስንመለከት በአብዛኛው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ ያመዘነ ሲሆን፤ በጥቂት የላይኛዉ ባሮ አኮቦ፣ በአብዛኛው ኦሞ ጊቤ እንዲሁም በጥቂት የመካከለኛው አባይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ ነበራቸዉ፡፡ የተቀሩት በአብዛኛው በበጋው ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ ስር ነበሩ (ካርታ 12) ፡፡

ካርታ 12 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

ጃንዋሪ የበጋ ወቅት የመጨረሻ ወር ሲሆን፤ በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ደረቃማው የአየር ጠባይ የሚስተዋልበት ጊዜ ቢሆንም፤ ከበልግ ወቅት መቃረብ ጋር ተያይዞ በመደበኛ ሁኔታ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል፣ የደቡብ፣ የምዕራብ፣ የመካከለኛውና የምሥራቅ ኦሮሚያ አንዳንድ ቦታዎች እንዲሁም የምሥራቅ አማራ ሥፍራዎች ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ።

በሚቀጥለው የጃንዋሪ ወር በብዙ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ጠባይ ጎልቶ እንደሚታይና በተለይም በአንዳንድ ደጋማ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ቀጣይነት ይረዋል፡፡ በሌላ በኩል አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት ከደመና ሽፋን መጨመር ጋር ተያይዞ  ከኦሮሚያ ክልል በሚገኙ በጥቂት የጅማ፣የኢሉባቦርና የምዕራብ ወለጋ ዞኖች፤ ከደቡብ ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል በሰገን ህዝቦች፣ ደቡብ ኦሞና ቤንች ማጂ ዞኖች፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል፤ በሲዳማ ክልል በተጨማሪም ከአማራ ክልል ሰሜንና ደቡብ ወሎ እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ይጠበቃል። የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ ሆነው ይቆያሉ።

# እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ የጃንዋሪ ወር ደረቃማው የአየር ጠባይ የሚስተዋል ሲሆንናበአብዛኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሰብል ስብሰባው ተጠናቅቆ የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራት በስፋት የሚስተዋልበት ወቅት ነው፡፡ እንዲሁም ከደረቃማው የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ የበጋው ወቅት የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ በቀጣይነት የሚስተዋልበት ጊዜ ነው፡፡

ከላይ በተሰጠዉ የአየር ሁኔታ ትንበያ መሰረት  የሚጠበቀው ደረቃማው የአየር ሁኔታ በመከናወን ላይ ለሚገኘው ድህረ ሰብል ስብሰባ እንቅስቃሴ በጎ ጎን ይኖረዋል፡፡ በአንጻሩም ከደረቃማው አየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ደጋማ አካባቢዎች ላይ ቅዝቃዜው በቀጣይነት እንደሚስታዋል የሚጠበቅ ሲሆን፤ እድገታቸውን ሙሉ ለሙሉ ባልጨረሱ ሰብሎች እንዲሁም

በመስኖ በመታገዝ በሚለሙ በፍራፍሬ ተክሎችና በጓሮ አትክልቶች ላይ አሉታዊ ጎን ሊኖረው ስለሚችል አርሶ አደሮች እነደ አካባቢው ሁኔታ የሚኖረውን ቅዝቃዜ ለማሻሻል የሚረዱ የተለመዱ ተግባራትን ለማከናወን የበኩላቸውን ቅድመ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ይመከራሉ፡፡  በአንፃሩ አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በተለይም በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅ፣ በመካከለኛዉ ደቡብ ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደቡባዊ ክፍል እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት ሊኖር እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ ይህም የሚገኘዉ እርጥበት  ከበልግ ወቅት መቃረብ ጋር ተያይዞ የበልግ እርሻን ቀድመው ለሚጀምሩ አካባቢዎች የአፈር ውስጥ እርጥበትን የሚያሻሽል እንዲሁም የማሳ ዝግጅትን አስቀድሞ ለማከናወን የጎላ ጠቀሜታ የሚኖረው ሲሆን፤ በተጨማሪም በደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ለሚገኙ የአርብቶ አደር አካባቢዎች የመጠጥ ውኃና የግጦሽ ሳር አቅርቦትን እንደሚያሻሽል ይጠበቃል፡፡

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪው ጃንዋሪ ወር የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ስንመለከት አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጠበታማ ሁኔታ እንደሚያገኙ ትንበያው ይጠቁማል፡፡ ከነዚህም መካከል የላይኛው ባሮ አኮቦ፣ የመካከለኛው እና የታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ ኦሞ ጊቤ፣ መካከለኛው ገናሌ ዳዋ እና ዋቤ ሸበሌ እንዲሁም በጥቂት የመካከለኛው አባይ ተፋሰሶች ናቸው፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ በአብዛኛው ቦታዎቻቸው ላይ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሆነው እንደሚቆዩ ይጠበቃል፡፡